የሰ/መ/ቁ 38811

የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ርሆቦት ሆሊሴቪየር ኃ/የተ/የግ/ማ ጠ/ተስፋዬ ክትላ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ አማረ አድማሱ ቀረቡ፡፡

## ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሥራ ክርክር ችሎት የጀመረ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚሁ ፍ/ቤት በቀረቡት ክስ አመልካች በህገ-ወጥ መንገድ የሥራ ውላቸውን ስላቋረጠው ወደ ስራ እንዲመልሣቸው የማይመልሳቸው ከሆነ ግን የተያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸውና የስራ ም/ወረቀት እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ላቀረበበት ክስ የስራ መሪ በመሆናቸው ክሱ በዚህ ፍ/ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት ከተቃወሙ በኋላ በድርጅቱ በደተረገው የመዋቅር በውስጥ የተጠሪ የስራ መደብ በመሠረዙና ተጠሪን ወደ ሌላ የስራ መደብ አዛውሮ ማሠራት ባለመቻሉ ማሠናበቱንና ይህም ስንብት ህጋዊ እርምጃ በመሆን የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም አመልካች የማስጠንቀቂያና የስራ ስንብት ክፍያ ለተጠሪ ፈጽሟል የም/ወረቅትም ሠጥቷል በማለት ለፍሬ ጉዳዩ መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ የሥራ መሪ የሚያከናውነው ተግባር ላይ የተሠማሩ ስለመሆናቸው ማስረጃ ስላላቀረበ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም የድርጅቱን ወጪ በመቀነስ የአመልካች የመደበኛ ት/ቤቶች ሀላፊነት የስራ መደብ መሠረዙን ያስረዳ ቢሆንም ተጠሪን ወደ ሌላ ቦታ አዛውሮ ማስረዳት አለመቻሉን የሚያስረዳ ማስረጃ ስላላቀረበ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ስለሆነም የ2 ወር ደመወዝ ከፍሎ ተጠሪን ወደ ስራቸው ይመልሣቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይርባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ስንብቱ ህገ-ወጥ በመሆኑ የ2 ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ ይመለሱ የሚለውን ውሣኔ ያፀና ሲሆን ነገር ግን አመልካች ለተጠሪ የ2 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የስንብት ክፍያ የከፈለ ለመሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ተጠሪ ወደ ስራ ከተመለሱ የተቀበሉትን ክፍያ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የአመልካች አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ተጠሪ የስራ መሪ ናቸው በተደረገው የመዋቅር መሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ የተሠረዘና ወደ ሌላ የስራ መደብ አዛወሮ ማሰራት ባለመቻሉ የስራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

ይህ የአመልካች አቤቱታ ለሠበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ጥቅምት 18/2001 የተፃፈ መልስ አቅርበዋል ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

በመጀመሪያ አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከት የተጠሪ የስራ ኃላፊነት የስራ መሪ የሚሠኛቸው ነው ወይስ አይደለም የሚለው በማስረጃ የሚረጋገጥ የፍሬ ነገር ጉዳይ እንደመሆኑ አመልካች ይህንኑ የማስረዳት ሸክም አለበት ነገር ግን ከመዝገቡ እንደተረዳነው በስር ፍ/ቤት አመልካች ይህንን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ የለም በመሆኑም በዚህ በኩል ያቀረበው የሠበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

ወደ ፍሬ ጉዳዩ ስንገባ አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን እንመለከታለን ተጠሪ ከስራ የተሠናበትኩት በህገ-ወጥ መንገድ ነው ሲሉ አመልካች ደግሞ በተደረገው የመዋቅር ማሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ በመሠረዙ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች የድርጅቱን ወጪ ለመቀነስ ባደረገው የመዋቅር ማሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ መሠረዙን አመልካች አስረድቷል የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን ካረጋገጡ በኋላ የሥራ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ያሉት አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ሥራ ማዛወር የማይችል መሆኑን አላስረዳም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28/1/መ/ መሠረት አንድ ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ከስራ የሚሠናበተው የያዘው የሥራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲሠረዝና ሠራተኛውን ወደ ሌላ ሥራ ማዛወር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ነው በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ የሥራ መደብ በመዋቅር ማሻሻል ምክንያት የተሠረዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የሥራ መደብ የተሠረዘው በበቂ ምክንያት ነው በሌላ በኩል ግን አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ የሥራ መደብ መዛወር አለመቻሉን የገለፁ ሲሆን ተጠሪ በቃራኒው አመልካች ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ ሊያሠራቸው የሚችል መሆኑን ገልፀው አልተከራከሩም በዚህ በሠበር ችሎት በሠጡት መልካም ቢሆን በአንቀፅ 28/1/መ/ መሠረት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ማስጠንቀቂያ ሊሠጣቸው ሲገባ አመልካች ማስጠንቀቂያ አለመሰጠቱ ስንብቱን ህገ-ወጥ ያደረገዋል በማለት ከሚከራከሩ በቀር በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተዛውረው ሊሠሩበት የሚችሉበት የሥራ መደብ እያለ የሥራ ውላቸው ሊቋረጥ እንደማይገባ ገልፀው አልተከራከሩም በመሆኑም ተጠሪው ይህንን ክርክር አንስተው ሣይከራከሩ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር አለመቻሉን አላስረዳም በሚል ምክንያት ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የደረሠበት መደምደሚያ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22889 በ26/05/2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 63104 በ4/10/2000 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

3/ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 28/1/ መሠረት በመሆኑ ህጋዊ ነው

4/ ተጠሪ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ከአመልካች የተቀበሉትን የማስጠንቀኪያ ጊዜ ክፍያ እና የሥራ ስንብት ክፍያ መልሠው ከሆነ አመልካቹ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ መልሠው ከሆነ አመልዛቹ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈላቸው የሥራ ምስክር ወረቀት ያልሠጣቸው ከሆነም እንዲሠጣቸው ተወስኗል፡፡

5/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት